# ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡

## ለቅዱሱ ኪዳን

## ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን!

## በጠቅላላም፡

## ለክቡራንና ክቡራት አንባቢዎቻችን!

---

*ሕያውና መለኮታዊ ስለኾነው፡ የግእዝ ቋንቋችንና የፊደል ገበታችን፡ እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያውያኑና በኢትዮጵያውያቱ ሕፃናት፥ በሞግዚት ወላጆቻቸውም መሣሪያነት፡ የፈጸመውን፡ ዕፁብና ድንቅ ተኣምራት፡ በመንፈሳዊ አትኵሮትና ተመሥጦ ኾናችሁ ትከታተሉት ዘንድ፥ ደግሞ፡ እናንተም፡ እያንዳንዳችሁ፡ ራሳችሁን፡ ለዚህ፡ የተቀደሰ በረከት፡ ታበቁ ዘንድ፡ ይኸው፡ የተኣምራቱን፡ የምሥራችና የትፍሥሕት ዜና፡ እንደሚከተለው አዘጋጅተን አቅርበንላችኋል።*

*በዚህ መልእክት፡ "ሞግዚት" የሚለው ቃል፡ ግእዙ፡ ወንዱን፡ "መግዝእ"፥ ሴቷን ደግሞ፡ "መግዝእት" ብሎ፡ በኹለት ጾታ የሚለያቸውን፡ ሐፀንት (ሕፃናት አሳዳጊዎች)ን የሚያጠቃልልና የሚወክል ይኾናል።*

## ዜና ተኣምር አንድ።

*"ስምን መልአክ ያወጣዋል"፥ ደግሞም፡ "እስመ ስሙ፡ ይመርኖ፡ ኀበ ግብሩ"፡ ማለትም፡ "የሰው ልጅ፡ መጠሪያ ስሙ/ሟ፡ ለተጠሪው/ዋ፡ የወደፊት ምግባር፡ አመላካች ነውና!" የሚሉት፡ መልካካም የኾኑ፡ ሃይማኖታውያን ይትበሃሎቻችን፡ ዛሬም፡ በእውነተኞቹ፡ ኢትዮጵያዊ፡ እመ-እግዚአብሔር ልጆች ዘንድ፡ አማናዊነታቸውና ሕያውነታቸው ተረጋግጧል።*

የመጀመሪያው ተኣምር የተፈጸመው፡ በተጸውዖ (መጠሪያ) ስሙ፡ “ፊደል” የተባለ፡ አንድ ኪዳናዊ ኢትዮጵያዊ ምእመንወካህን፡ የዐደራ ልጁን፡ በአቅራቢያቸው ወዳለ፡ ባንድ፡ አጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ወደሚገኝ፡ የአብነት ትምህርት ቤት፡ ፊደል ለማስቈጠር፡ ይወስደዋል።

በዚያም ሣለ፡ አስቀድሞ፡ ከአብነት ትምህርት ቤት “መምህሩ” ጋር፡ ስለግእዙ አሌፋት መወያየት ስለነበረበት፡ መምህሩን አግኝቶ፡ ስለመልክአ ፊደላቱ፡ አማናዊና ቀጥተኛ የንግግር ድምፃቸው ይወያያል፤ በሚወያዩበት ጊዜም፡ ይኸው ኪዳናዊ ሞግዚት፡ ልጁን፡ በቤቱ ሲያስጠናና ሲያስተምር፡ የመጀመሪያዋን፡ የግእዝ አሌፍ፡ “አ”፡ ድምጡ፡ በደረቁ የሚነገር ኾኖ፡ እንደ“ኧ” ያለ በመኾኑ፡ ያን፡ ቀጥተኛ ሥርዓት ስለሚከተል፡ *“መምህሩም፡ ልጁን፡ በዚያው ዓይነት እንዲያስተምሩለት”* ይጠይቃቸዋል።

የአብነት መምህሩም፡- *“እንዲህ ያለውን ትምህርት፡ ከየት እንዳገኘ”* ይህን፡ ኪዳናዊ ሞግዚት፡ ይጠይቁታል።

እርሱም፡ *“ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ ከተባሉ፡ አንድ፡ ኢትዮጵያዊ ካህን፡ በቃል እንደሰማውና ከመጽሐፋቸውም እንዳገኘው”፡ ለመምህሩ ያስረዳቸዋል።*

በዚህ ጊዜ፡ መምህሩ፡ “ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ”፡ የተባሉትን ካህን፡ ያዉቋቸው ኖሮ፡ *“አይ! ያማ፡ ትክክል አይደለም፤ ደግሞ፡ ትክክል ቢኾንም እንኳ፡ አኹን፡ ጊዜው ስላለፈበትና ኹሉም የሚጠቀመው፡ በአንድ፡ ተመሳሳይ ድምፅ ብቻ ስለኾነ፡ በዚያው መቀጠል እንዳለበት”* ለኪዳናዊው ሞግዚት፡ ከአጽንዖት ጋር ያስታውቁታል።

በዚህን ጊዜ፡ ኪዳናዊው ሞግዚት፡ በእርሱ በኩል ያደረገው ጥረት፡ ያልተሳካ መኾኑን ሲያውቀውና ሲረዳው፡ ተስፋውን፡ በእግዚአብሔር ላይ ጥሎ፡ የክህነት ባልደረቦቹ የኾኑትን፡ የቃል ኪዳን ባለቤቱንና እኅቱን፡ ከሕፃን ልጁ ጋር፡ በትምህርቱ ጉባኤ ላይ እንዲገኙ በማድረግ፡ እርሱ ግን፡ ለብቻው፡ ወደቤቱ ያቀናል።

ከዚህ በኋላ፡ በአብነት መምህሩ፡ ትምህርቱ ይጀመራል።

*መምህሩም፡ ፊደል ማስቆጠሩን፡* «*"ሀ! ሁ! ሂ! ሃ! ሄ! ህ! ሆ!"*፡ ብለው፡ ግእዝ የኾነውን፡ የመጀመሪያውን፡ የ"ሀ"ን አሌፍና ራብዕ የኾነውን፡ የአራተኛውን፡ የ"ሃ"ን አሌፍ፡ በአንድ፡ ተመሳሳይ፡ የራብዑ ድምጻቸው፡ *ማለትም፡ አፍ በሚያስከፍት፡ የንግግር ድምጡ "ሃ!"* ብለው፡ ማሰማት ቀጠሉ።»

በዚህ ጊዜ፡ ከኪዳናዊው ሞግዚት ጋር፡ ምንም ዓይነት መተዋወቅና መቀራረብ የሌለው፡ አንዱ፡ ታዳጊ ሕፃን፡ በትምህርቱ ጉባኤ ላይ፡ መምህሩን፡-

*«ኹለት ጊዜ፡ "ሃ! ሃ!" የምንለው፡ ለምንድር ነው? ኹለት፡ ተመሳሳይ "ሃ!" ነው ያለው?»* ብሎ፡ ይጠይቃቸዋል፤ ያፋጥጣቸዋል።

በዚህ ጊዜ፡ መምህሩ፡ ምንድር ምላሽ ይስጡ?!

ባለቅኔው፡ *"አዬ! መምህር፡ ያለበት አባዜ፤*

*አስተዋይ ተማሪ፡ ባጋጠመው ጊዜ!"* ብሎ፡ የተቀኘው ለእንዴህ ዓይነቱ፡ ገጠመኝ ይመስላል።

ኢትዮጵያዊው ብሂል፡ "ንግባእኬ፡ ኀበ ጥንተ ነገር!" እንዲል፡ እኛም፡ መነሻ ወደኾነን፡ ወደቀድሞ አርእስተ ነገራችን እንመለስና፡ ከዚህ በኋላ የኾነውንና የተከሠተውን፡ ዜና ተኣምር፡ እንግለጽላችሁ!

አዎን! ከዚህ በኋላ የኾነውማ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ መምህሩን፡ ፊታቸውን አጸፍቶ፥ አፋቸውንም አስከፍቶ፡- *«አይ የለም! "ሀ"፡ የተባለው፡ የመጀመሪያው አሌፍ፡ ድምፁ፡ አፍን ሳያስከፍት፡ በደረቁ የሚነገር ኾኖ፡ እንደ"ሽ" የሚነበብ ሲኾን፥ ሌላኛውና ራብዑ "ሃ" ደግሞ፡ አፍን በመክፈት፡ የሚነበብና የሚነገር ነው!"»* ሲል፡ ቀጥተኛውንና ትክክለኛውን ምላሽ፡ እንዲሰጡ አድርጓል።

እዚህ ላይ፡ ግእዝ፡ የተፈጥሮ ቋንቋ ለመኾኑ፡ አንዱ ማመሳከሪያ፡ ሰዎች፡ የሥጋ አካላቸው በሚደክምበትና በሚዝልበት ጊዜ፡ ሲያዛጉ፡ "ኣ...ኣ...ኣ!"፡ ብለው፡ እንደ"ኣ" ፊደል፡ አፋቸውን በመክፈት፥ ወይም፡ ራሷን፡ የ"ኣ"ን ፊደል የሚጠቀሟት፡ መኾኑ ነው።

## ዜና ተአምር ኹለት።

ሌላውና ኹለተኛው ተአምር፡ የተፈጸመውና የተከሠተው ደግሞ፡ በኪዳናዊው ወንድማችን፡ በሕፃን አቤሜሌክ ነው።

ያም፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሕፃናት፡ “፬ ዓመት፡ ከ፬ ወር፡ ከ፬ ቀን” ሳይሞላቸው፡ ትምህርት እንዳይጀምሩ፡ በባዕዳን ጠላቶቻችን አማካይነት ተወስኖባቸው፡ ለብዙ፡ መቶ ዓመታት፡ የዚያ፡ ሰይጣናዊ ዕቅድ፡ ሰለባ መኾናቸው፡ ይታወቃል።

ታዲያ! ይህን፡ ሰይጣናዊ ሤራ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ረቂቅ፡ እውቀትና ኃይል፡ አስቀድሞ የተረዳው፡ ኪዳናዊው ሞግዚት፡ ንቡረ-እድ ኤርምያስ፡ የልጅ ልጁ የኾነውን፡ ሕፃን አቤሜሌክን፡ ገና፡ አፍ መክፈትና መናገር ባልጀመረበት፡ የዐራስነት ጨቅላነቱ፡ ፊደል ማስቈጠር ይጀምራል።

የግእዙን አሌፋት፡ ኢትዮጵያኛውን ጨምሮ፡ መልክአ ፊደላቱንና ኅርመታቱን፥ አኀዛቱንም (ቊጥሮቹንም)፡ በሥዕላዊ መልካቸው፡ በክርታስ ላይ ዐትሞ፡ ሕፃኑ፡ በሚመገብበት፡ መንበረ ገበታ (ጠረጴዛ)፥ በሚጫወትበት፡ መዳኺያ መርሕብ (ዳዴ በሚልበት ቦታ)ና በሚተኛበት፡ ምስካበ (መኃደሚያ) መደቡ ላይ፡ አስቀምጦ፡ በዓይኑ፡ እንዲመለከታቸው፥ የስያሜ ድምጻቸውንም፡ እንዲሰማ እያደረገ ይቆያል።

ታዲያ! ይኸው ሕፃን፡ ከአፍ መፍታት ዕድሜው ደርሶ ኖሮ፡ በዚያን ጊዜ፡ ቤተሰቡ በሚኖሩበት፡ የባሕር ማዶ ግዛት፡ ባንድ ወቅት፡ ቀጠሮ በተያዘለት ዕለት፡ ከወላጅ አሳዳጊዪቱ ጋር ኾኖ፡ የሕፃንነት ሓኪሙ ወደምትገኝበት፡ የግል የሕፃናት ቤተ ሕክምና ይኼዳል።

በዚያም፡ እግዚአብሔር ባወቀ፡ ሓኪሟ፡ ኢትዮጵያዊት በመኾኗ፡ እርሷን ለማየት፡ ተራው ቀርቦ፡ እስኪጠራ ድረስ፡ በሚጠባበቅበት፡ የሕጻናት መጫወቻ እልፍኝ ግድግዳ ላይ የተሰቀለ፡ የኢትዮጵያን የፊደል ገበታ ይመለከታል።

በዚህን ጊዜ፡ ሕፃኑ አቤሜሌክ፡ በፊደል ገበታው ላይ የሠፈሩትን የፊደላቱን መልክአት፥ በንግግር ድምጥ፡ ተለይተው የሚታወቁበትንም ስማቸውን፡ በዐራስነቱ ወቅት፡ ከማየትና ከመስማት በቀር፡ ማንም መምህር፡ እያስተካከለና እያረመ፥ እየመራና "እንዲህም በል!" እያለ፡ ያላስተማረውን፡ ገና፡ በዚያ፡ የአንድ ዓመት ከመንፈቅ፡ የሕፃንነት ዕድሜው፡ የአሌፋቱንና የአኀዛቱን መልክአት፡ አንድ በአንድ እየለየና እየቈጠረ፡ በትክክለኛውና በቀጥተኛው የንግግር ድምጣቸው፡ አፉን ከፍቶ፡ ማንነታቸውን ማስሰማት ጀመረ።

ዐብራው የነበረችው፡ ወላጅ ሞግዚቱም፡ በድንጋጤ ተገርማ፡ ማመን ያቃታትን፡ ያን ትንግርት፡ ወደቤት ከተመለሰች በኋላ፡ ለመላው ቤተሰብ አበሠረች፤ እነርሱም፡ ሕፃን አቤሜሌክ፡ ፊደላቱንና አኀዛቱን የያዘውን ጥራዝ አንሥቶ፡ እያገላበጠ፡ ማንም ሳይነግረው፡ በገዛ ራሱ፡ በየስማቸው ሲጠራቸው እስኪሰሙና እስኪያዩ ድረስ፡ ትንግርቱ፡ እውነት መኾኑን ለማመን፥ ለማረጋገጥም ከብዷቸው ነበር።

አዎን! እጅግ ይገርማል፤ ይደንቃልም፤ እግዚአብሔር ይመስገን። በሕፃናቱ፡ የእውቀትና የዕድገት መጽሓፍ መግቢያ ውስጥ፡ ይህን የሥራ አካኼድ በተመለከተ፡ በጽሑፍ የሠፈረው፡ መመሪያ፡ እንዲህ፡ በተግባር ላይ ውሎና ጣፋጩን ፍሬ አስገኝቶ መመልከቱ፡ የቱን ያህል እንደሚያስደስትና እንደሚያረካ፡ ለማንም ግልጥ ነው።

እንግዴህ፡ ይህ የኾነው፡ ገና፡ አፍ ያልፈቱ ሕፃናት፡ የፊደላቱንና የአኀዛቱን ኅርመታዊ መልክና የስም አጠራራቸውን፡ በጆሮአቸው፡ በድምጥ፡ በሚሰሙበት፥ በዓይናቸውም፡ በሚመለከቱበት ጊዜ፡ "እወዲ ሕግየ፡ ውስተ ልቦሙ፤ ወእጽሕፎ፡ ውስተ ኅሊናሆሙ"፡ ማለትም፡ "ሕጌን፡ በልቡናቸው አሳድራለሁ፤ በኅሊናቸውም እጽፈዋለሁ" ካለው፡ በአጽባዕተ እግዚአብሔር፡ ከተሣለውና ከተቀረጸው፡ መለኮታዊ አሌፋት ጋር፡ እንደድርና ማግ ስለሚዋደድ፥ ስለሚዋሓድም ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ ሕፃናቱ፡ አፍ መፍታት በሚጀምሩበት ጊዜ፡ በቀላሉ፡ ያለማንም ርዳታ፡ ፊደላቱን ማጋዝና ወደምንባብ መግባት ኹሉ ይቻላቸዋል። (ኤር. ፴፩፥ ፴፩-፴፬።)

## ዜና ተኣምር ሦስት።

ይህ፡ ሦስተኛው ተኣምር፡ የተፈጸመው ደግሞ፡ የዛሬ፡ ኹለት ሺህ ዓመታት ገደማ፡ በሕፃናቱ ርዕሰ መምህር፡ በሕፃን፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ሕፃን ኢየሱስ መሲሕ፡ በ፳ ዓመቱ፡ በእናቲቱ ማርያም ሕፅን (ዕቅፍ) ኾኖ፡ ወደትምህርት ቤት ይገባል። የኔታውም፡ "አ፡ አሌፍ!"፥ "በ፡ ቤት!" እያለ፡ ፊደል ሲያስቈጥረውና ሲያግዘው፡ እርሱም፡ አስከትሎ፡ የኔታውን፡- "ምንት፡ ትርጓሜሁ ለአልፍ?" ማለትም፡ "አ ብለህ፡ 'አልፍ' ያልኸው ቃል፡ ትርጓሜው፡ ምንድር ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል።

የኔታው፡ "ይህን ምሥጢር ለመፍታት፡ ለእኔ፡ ዓቅሙ፡ እንዴት ይኖረኛል?" በሚል ስሜት፡ ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ መስጠቱ፡ ሳይቻለው በቀረ ጊዜ፡ ሕፃን መሲሕ ኢየሱስ፡ "አነ ውእቱ፡ አልፍ ወኦ! አነ ቀዳማዊ፥ ወአነ ደኃራዊ! ርእስ፥ ወማኅለቅት!"

ማለትም፡ በነጠላ ትርጓሜው፡-

«"በቃልነቱ፡ ለማንነቱ መገለጫ፡ መነሻ እንደኾነው፡ እንደ'አ' እና መዳረሻው እንደኾነው፡ እንደ'አ' አሌፋት፡ እኔ፡ ፊተኛው እና ኋለኛው፥ መጀመሪያው እና መጨረሻው ነኝ!"

በድርብ፡ ምሥጢራዊ ትርጓሜው ደግሞ፡-

"'አልፍ' በተሰኘሁበት፡ በ'አ'፡ አብወእም'ነቴ፥ በ'ል'፡ ወልድነቴና በ'ፍ'፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ሦስትነቴ፡ እንደ 'አ' ፊደል፡ አንድ ለኾንሁበት፡ ቅድስት ሥላሴነቴ፡ ቀዳሚ ፊተኛና ተከታይ ኋለኛ፥ ጥንት መነሻና ፍጻሜ ማለቂያ፡ የሌለኝ፡ እኔ ነኝ!" ማለቱ ነው።» ሲል ተርጉሞለታል። (ራእ. ፳፪፥ ፲፫።)

አዎን! እንግዴህ፡ እነዚህ ኹሉ ተኣምራት፡ የሚያመለክቱንና የሚያስገነዝቡን፡ ኢትዮጵያዊው ነቢየ እግዚአብሔር፡ ኢሳይያስ፡ "ኵሉ ደቂቅኪ፡ ምሁራን፥ ወምሁራት፡ በኀበ እግዚአብሔር!"፡

ማለትም፡ ‘‘ልጆችሽም ኹሉ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተማሩ ይኾናሉ!’’ ያለው፡ አምላካዊ ቃል፡ በኢትዮጵያዋ እመ እግዚአብሔር ድንግል ማርያም፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቿ ዘንድ፡ ከሥነ-ፍጥረት ልደት አንሥቶ፡ እስከዘለዓለም ድረስ፡ ጸንቶ የሚሠራና የሚቀጥል መኾኑን ነው። (ኢሳ. ፶፬፥ ፲፫፤ ኤር. ፴፩፥ ፴፫-፴፬፤ ዮሐ. ፮፥ ፵፭።)

\+ + +